# ደወል ተደወለ!

ተነሳ ትመመው በያደባባዩ፤
አርበኝነትህን ጀግንነትህን ይዩ፤
ለነጻነት ተነስ ለአርነትህ፤
ከትከሻህ አውርድ ባርነት ይቅርብህ!!!

አንድ ባንድ ነጥቆ፤
በእስር አምቆ፤
እንዲህ እያፈነህ፤
መኖሩ ይቅርብህ፤
ለነጻነት ተነስ፤
ለድልህም ገስግስ።

እየለቃቀመ በተራ በተራ፤
ደምእያፈሰሰ በላይህ ሲያጎራ፤
ምን ትጠብቃለህ፤
በቁምህ ሲቀብርህ፤
እርሱ እየደላው መከራ ሲግትህ።

ምን ጎደለው እርሱ፤
ቁንጣን መደገሱ፤
አንተን ነው የከፋህ፤
መከራ ያመሰህ።

ተዋርዶ ከመኖር፤
ተከብሮ ማደር፡
ይበልጣል ይሻላል፤
የመከራ ኑሮ ይቅር ይበቃሀል።

የሚመራህ አጥተህ፣
ሰብሳቢ ቢጎልህ፣
በጎበዝ አለቃ ታገል ተጠናክረህ።
የአምስት አመቱ አረበኛ ታሪክህ፣
የጣሊያን ጭካኔን በድል ማባረርህ፣
ምስክር መረጃ አለኝታ ይሁንህ።
ዱሮም አለመድክም ነጻነት ነው ክብርህ፣
በባርነት ማደር ማጎብደድ አይበጅህ።

**ተነሳ ትመመው በያደባባዩ፣**
**አርበኝነትህን ጀግንነትህን ይዩ፣**
**ለነጻነት ተነስ ለአርነትህ፣**
**ከትከሻህ አውርድ ባርነት ይቅርብህ!!!**

ትግስትን ሞኝነት፣
ማስተዋልክን ንቀት፣
እሰከ መቼ ድረስ፣
በጭካሌ ይንገሥ፣
ናድና ገርስሰው አንቅርና ትፋው፣
የተሻለ እንጂ የባሰ ላታየው።

ይበቃል ተነሳ የመከራ ኑሮ፣
ከመሰቃየቱ እጅናግርህ ታስሮ
እንዳትሞት እንዳትሽር በደረቅ ጉሮሮ፣
መከራ በዝቶብህ በደልህም ንሮ፣
ተነሳ መንግለው ይበቃል እሮሮ።

እንደዶሮ ጫጬት እንድ ባንድ ለቅሞ፣
ልጆችህ አለቁ ምን ተረፈህ ከርሞ።
ገድሎ አኮላሽት አላሽቆ አዳክሞ፣
ባንተ እየደለቀ የመከራ አታሞ፣
ሃያ አመት ሆነው መርዝህን ቀምሞ።

መሬቱ ያንተነው፡
በከርሷ ውስጥ ያለው፣
ሀብትና ንብረቱ፣
ያለው ባገሪቱ፣
ወታደሩ ሳይቀር፣
ሁሉም ሲደማመር፣
አንጡራ ሀብትህ ነው
ያነተው ነው፣ያንተው ነው።

ግብር እየከፈልህ፣
ተርበህ ባሳደርህ፣
ልጆጭህን ነጥቆ፣
ጠብመንጃ አስታጥቆ፣
መሬትህን ሰርቆ፣
ለባእድ ሸምቆ፣
ደግሞ ተመልሶ አንተን ከበደለህ፣
በእብሪት በንቀት ወደስር ካጋዘህ፣
አባሮ አሳዶ በግፍ ከገደለህ፣
ከዚህ የበለጠ ምንስ ሊመጣብህ፣
በቃ ይበቃሀል ተነሳ አብረህ።

**ተነሳ ትመመው በያደባባዩ፤**

**አርበኝነትህን ጀግንነትህን ይዩ፤**

**ለነጻነት ተነስ ለአርነትህ፤**

**ከትከሻህ አውርድ ባርነት ይቅርብህ!!!**

አርሱ ተዘጋጅቷል፤

መዝብሮህ አውጥቷል፤

አንጡራ ሀብትህን፤

ሳይቀር እርዳታህን፤

ስጋህን አላምጦ፤

አጥንትህን ግጦ፤

ለመከራ ገልጦ፤

ተዘጋጅቷል ጥሎህ፤

ለመሮጥ በትኖህ፤

የአህያ ፈሊጥ ተረት ተርቶብህ።

ተነሳና ታገል ምንም አይቀርብህ፤

መሞትም ከሆነ ከመሞት በቁምህ፤

ክብርን ልበስላ ሰውነትህ ታውቆ፤

መስዋእትን ከፍሎ ዘልቆ ተጠናቆ፤

ነጻነት ለመኖር በድል አሽብርቆ።

ተነስ! ተነስ! ተነስ! ተነስ! ይበቃሀል፤

በባርነት ኑሮ ሳትሞት ገሎሀል፤

በመከራ ኖሮ በቁምህ ቀብሮሀል፤

አትሰማ አትለማ ቀፍድዶ አስሮሀል፤

አፍኖና ረግጦ ግፍ አዝንቦብሀል፤

የመከራ ኑሮ ከእንግዲህ ይበቃል።

**ተነሳ ትመመው በያደባባዩ፤**

**አርበኝነትህን ጀግንነትህን ይዩ፤**

**ለነጻነት ተነስ ለአርነትህ፤**

**ከትከሻህ አውርድ ባርነት ይቅርብህ!!!**

ሆ!!!!! ብለህ ተነሳ፤

አግሳ እንዳንበሳ፤

ፈሪውን ይጭነቀው፤

ወኔውንም ይሸናው፤

አርብኝነትህን ድገምና አሳየው።

ከልኩ ካለፍ መጠን ገደብ ካጣ፤

በዘረጋወ ወጥመድ ራሱ እንደሚቀጣ፤

በሕዝብ ላይ እንዲህ፤

እብሪት ካባዘብህ፤

ይቅመስ ማንነትክን ተዋደቅ ለክብርህ።

ጉዱ ጉዳጉዱ በይፋ ተገልጧል፡

ለምንም አይበጅህ ክህደት ተክዷል፤

ለጥፋት መቆሙ በየመስኩ ታይቷል፤

በይፋ ሌላውን የሌለን ይሰብካል።

ከቀን ወራት ብለህ፤

ካመት አስር ቆጥረህ፤

ሃያውን ደፍኖብህ፤

የተሻለ ኑሮ በጉጉት ጠብቀህ፤

ግፍ እያዘነመ ባርነት ጭኖብህ፤

ከዚህስ የባሰ ምን እንዳይመጣብህ፤

ደምህን አዝርቶ እንባህን ሲግትህ።

ተነሳ ትመመው በያደባባዩ፤

አርበኝነትህን ጀግንነትህን ይዩ፤

ለነጻነት ተነስ ለአርነትህ፤

ከትከሻህ አውርድ ባርነት ይቅርብህ!!!

ኑሮህ አሽቆልቁሏል፤

ኢኮኖሚው ታሟል፤

በርሱ እጅ አይሽርም፤

ማገገም አይችልም፤

ከውሸቱ ብዛት፥

እድገቱ ነው ውድቀት።

ሊታምነው ከዳዳህ፤

ይህን ሁሉ እያየህ፥

በጎ እያለሁ ብለህ፤

እጅህን ከሰጠህ፤

ለሚደርሰው ሁሉ በራስህ አመጣህ።

ሁሉም በያለበት በውስጥም በውጭም፤

መናቆር አይበጅም፤ለምንም አይጠቅምም፤

ያለፈውን እንተው፤

መልካሙን እናርባው።

ሕዝብ እየሰቀየ በደሉ በዝቶበት፥

በሆነ ባለሆነው ምን ይበጃል ሙግት፤

ቀናትም አይደሉ አለፉ አመታት።

ባንድነት ተነሳ አቅም አሰባስበህ፤

የህዝብና ታሪክ አደራ አለብህ።

ተነሳ ትመመው በያደባባዩ፤

አርበኝነትህን ጀግንነትህን ይዩ፤

ለነጻነት ተነስ ለአርነትህ፤

ከትከሻህ አውርድ ባርነት ይቅርብህ!!!

ታምሩ ድልነሳ!

April 3, 2013